በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የ6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሞዴል ፈተና

ሽየ፲፯ ዓ/ም

አጠቃላይ ትእዛዝ

የተፈቀደ ሰአት ፡- 1ሰአት
የጥያቄው ብዛት 40

ውድ ተፈታኞቻችን ይህ የአማርኛ ቋንቋ ት/ት ፈተና ነው በዚህ ፈተና ውስጥ 40 **ጥያቄዎች ተካተዋል ለእያንዳንድ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን ምርጫ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫው በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል ። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደ ቦታ በሙሉ በሚታይ መልክ በደንብ መጥቆር አለበት የጠቆረውን ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጸዳት አለበት።።**

ፈተናውን ሠርቶ ለመጨረስ የተፈቀደ ሠአት 1 **አንድ ሰአት ነው ።።ሠርቶ ለመመለስ የተሰጠው ሠአት ሲያበቃ የምንጠቀምበትን መፃፍያ እርሳስ ማስቀመጥ ና ፈተናው መስራት ማቆም አለባችሁ ። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ(ኟ) እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ ተቀምጣችሁ መጠበቅ አለባችህ ።**

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናውን ህግ የማያከብር ተፈረታኝ ፈተናው አይያዝለትም ፈተናውን እንዳይፈተን ይደረጋል ።

ፈተንው መስራት ከመጀመራችሁ በፊት መልስ መስጫ ላያ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት ።

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !!

ምንባብ

የሠው ልጅ ***አካላዊ መለያ*** እንዳለው ሁሉ ማንነቱን የሚገልፅበትና የሚለይበት ባህል አለው ::አንድ ህዝብም ማንነቱን ለመግለፅና ለመለየት የሚችለው በባህሉ አማካኝነት ነው::

ባህል አንድን ብሄር ብሄረሰብን ወይም ህዝብን የአንድ አገር ዜጋ አድርጎ ለማቅረብ የሚያገለግል ***ወሳኝ መሳርያ*** ነው ::በሌላ በኩል ደግሞ የተለያየ ሕዝቦች የሚኖሩበት አንድ አገር ከሌሎች አገሮች መለያ የወል ህልውን ማረጋገጫ ክስተት ነው::

አገራችን ኢትዮጵያ ***የሺየሌ*** እፅብ ድንቅ ባህሎች ባለቤት ናት ከዚህ አኳያ ***ውጫዊ ገፅታውን*** በማየት ለዘመናት የብሔረሰቦች መዚየም እየተባለች ስትጠራ ኖራለች በውስጣዊ ገፅታዊ የተለያዩ ባህሎች ***ተጣጥመው*** የሚገዙበትን ፈር በመክፈት ሠብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚጠበቁበትን ኢትዮጵያ ለመገንባት አስተማማኝ ምልክት እየፈነጠቀ ያለብት ወቅት ቢኖር አሁን ነው::

ባህሎች ተጣጥመው እንዲስተናገዱ ማድረግ መቼውም ቢሆን ቀላል ሆኖ አያቅም በአለንበት ዘመን በአገር ደረጃ የተዋቀረ ህብረት የዜጎችን ባህላዊ ማንነት የማክበርና የማስከበር ሀላፊነት አለበት ይህ ሲሆን ባህል የሰው ልጅ ገንቢ ተግባሩን እንዲያከናውን የሚያደርጉትን መሰናክሎች በማስወገድ በኢኮኖሚና ፓለቲክዊ መስክ መደጋገፍና መቻቻልን መፍጠር ያስችላል

ምንጭ የባህል መፅሀፍ 1988 እትም ተሸሽሎ የቀረበ

መምርያ አንድ ፡- ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሰባት ያሉ ጥያቄዎች ምንባብ መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው ስለሆነም ምንባቡን በጥሞና በማንበብ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱን በመልስ በመስጫ ላይ አጥቁሩ

1. ‹‹አካላዊ መለያ›› ለሚለው ሀረግ አቻ ፍቺ ---------- ነው::

ሀ. መልክአ ምድር ለ. ቁሳዊ
ሐ. የሰውነት ክፍል መ. የራስ የሆነ መልከ ና አቋም

2. ወሳኝ መሣሪያ ነው ሲል ---------- ማለት ነው::

ሀ. ዋነኛ መሰርያ ነው ለ. ውሳኔ ሠጪ ክፍል ነው
ሐ. የህልውና ማረጋገጫ ነው መ. አገልግሎት ሠጪ ነው

3. ስለ ባህል ከተነገሩ ሀሰቦች ጋር ***የማይስማማው*** አባባል የቱ ነው::

ሀ. ባህል የማንነት መግለጫ ነው
ለ. ባህል አንድን ህዝብ ዜጋ አድርጎለማቅረብ የሚችል መሳርያ ነው::
ሐ. ባህሎች ተጣጥመው እንዲስተናገዱ ማድረግ አይቸልም
መ. ባህል ቁሳዊ መንፈሳዊ ተብሎ ኪከፈል ይችላል

4. ‹‹ውጫዊ ገፅታ›› ¨ ለሚለው ተቀራራቢ ፍቺ የቱ ነው

ሀ. ለውጭ ሀገር ሠው የሚታይ ለ. የቆዳ ሽፋን ሐ. መልክ መ. የላይላዩ ሁኔታ

5. ‹‹አያሌ ›› ሲል ---------- ማለቱ ነው፡፡

ሀ. ኃያላን ለ. ብዙ ሐ. ቁጥራቸው ያልተወቀ መ. ከፍተኛ

6. ተጣጥመው ለሚለው ፍቺ የሚሆ ነው፡

ሀ. ተግባብተው ለ. ተለያይተው ሐ. ተጎሻሸመው መ. ተወያይተው

7. የሁለተኛው አንቀፅ ዋና ዓረፍተ ነገር .....ላይ ይገኛል
ሀ.መጀመሪያ ለ.መጨረሻ ሐ.መሃል ላይ መ. መለመሪያና መጨረሻ
<u>መመሪያ ሁለት</u>

ከተራ ቁጥር ስምንት እስከ አርባ ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል እያንዳንዱ ጥያቄ በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሆነውን መልስ ምረጡ ::

8. .....ትርጉም አዘል የሆነ የመጨረሻ የቋንቋ ንዑስ ክፍል ነው

ሀ. ነፃ ምዕላድ ለ. ጥገኛ ምዕላድ ሐ. ምዕላድ መ. ሁሉም መልስ ነው

9. አንቀፅ ስንት ተዋቃሪ አካላት አሉት

ሀ. አራት ለ. ሁለት ሐ. አንድ መ. ሦስት

10. ‹‹ልማዳችን ›› የሚለው ቃል በምዕላድ ተከፍሎ ሲፃፍ የሚያሳየው የቱ ነው ::

ሀ. ልምድ-አች ለ. ልምዳ- ችን ሐ. ልምዳች -ን መ. ልምድ-ኣችን

11.በሀይለ ቃሉ መነሻነት የተለያዩ ምሳሌዎችን መረጃዎችን በማቅረብ ሀሳብን ለማብራራት የሚጠቅም ነው፡፡

ሀ. መዘርዝራዊ አርፍተ ነገር ለ. አንቀፅ ሐ. ሀይለ ቃል መ. መልስ የለም

12.እንደየ እድሜ ደረጃችን የባህል <u>ሰሻራ</u> ያረፈባቸው ልብሶች አሉን፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ --- ነው፡፡

ሀ. የእጅ መፃፍ ለ. አስፋፍ ሐ. ምልክት መ. አለባበስ

13. በጫካው ውስጥ በርካታ *እንስሳት* ይኖራሉ።የተሰመረበት ቃል ---------- ነው።

ሀ. የተፀውዖ ሥም ለ. የወል ስም ሐ. ረቂቅ ስም መ. የነገር ሥም

14. ከዚህ በታች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ነፃ ምእላድ የሆነው የቱ ነው።

ሀ. ክፍላችን ለ. አሸዋማ ሐ. ትምህርት መ. ጠለፈች

15.በሬው ቀናበል ከጥጉ ድረስ

አርሶ ያበላ ----------።ለዚህ ግጥም መሙያ የሚሆነው ሀረግ ---------- ነው

ሀ. ከንፈር አያወላ ለ. ለዚህ ቤት እንግዳ ሐ. የግራሩን ስር መ. አለው የደስደስ

16.ኢትዩጵያውያን *ታትውፊታቸው* ከሚቀዳ አለባበስ አንዱ ሀገርኛ ቀሚስ ነው።የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ

ሀ. ከባህላቸው ለ. ከትውልድ ሲተላለፍ የመጣ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው መ. ከተፈጥሮ አቸው

17. አንድ ነጠላ ሀሳብን ለመግለፅ የሚያገለግል አነስተኛ የፅሁፍ ክፍል

ሀ. አንቀፅ ለ. ድርሰት ሐ. ቃል መ. ሐረግ

18.ቃላዊ ግጥም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ---------- ነው።

ሀ. የግጥም ፀሁፍ ለ. ቃላዊ ፈጠራ ሐ. ድርሰት መ. ሁሉም መልስ ነው

19.ከተዘጋጀ በኋላ በተፈለገው መንገድ ሀሳብን በትክክል መስፈሩን የሚያሣያ ንድፍ ነው።

ሀ. ዓረፍተ ነገር ለ. አንቀፅ ሐ. ዋና እረፍተ ነገር መ. ቢጋራ

20.የሽመና ባለሙያዎች የሚያመርቱትን ወደ ልብስነት የሚለውጡት በራሣችን *ጥበብ* ነው።

ሀ. አካሄድ ለ. ስሜት ሐ. እውቀት መ. ሀገርኛ

21.የቃላት ተመሣሣይ ፍቺ ማለት ---------- ነው።

ሀ. ተቃራኒ ፍቺ ለ. አቻ ፍቺ ሐ. በትርጉም የሚቀርብ ፍቺ መ. ሁሉም መልስ ነው

22.....አንድ ነገር መቼ እደተከሰተ ወይም እደሚከሰተ ይገለፃል

ሀ. የጊዜ ተውሳክ ግስ ለ.የሁኔታ ተውሳክግስ ሐ.ተውሳክግስ መ.መልስ የለም

23.በወሩ *መባቻ* ላይ እመጣለሁ ።የተሰመረበትን ቃል የሚገልፀው ።

ሀ. መጀመሪያ ለ. መጨረሻ ሐ. መካከል መ. እንደ አጋጣሚ

24.ሰናይት ወደ ባህር ዳር እየሄደች ነው የትኛውን የጊዜ አይነት ያመለክታል።

ሀ. ሀላፊ ጊዜ ለ. የትንቢት ጊዜ ሐ. የአሁን ጊዜ መ. ተደጋጋሚ ጊዜ

25.ከሚከተሉት ሥርአተ ነጥቦች ሠአትን ከደቂቃ ለመለየት የሚያገለግለው የቱ ነው።

ሀ. ፡ ለ. ፣ ሐ. ፤ መ. /

26.ሁለት ያለቁ ሀሣቦችን አጣምሮ ለማስቀመጥ የሚያገለገል ሥርአተ ነጥብ

ሀ. ነጠብጣብ(. . .) ለ. ነጠላ ሠረዝ (፣) ሐ. ትምህርተ ጥቅስ(‹‹ ››) መ. (፤)ድርብ ዘረዝ

27.ወይም የሚለውቃል ተክቶ ሊገባ የሚችለው ስርዓተ ነጥብ .....ነው

ሀ.እዝባር ለ. ቅንፍ ሐ. ይዘት መ. ነጠብጣብ

28.ለአርፍተ ነገር ውስጥ በማሠሪያ አንቀፅነት የሚያገለግለው

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ተውሳ ግስ መ. ባለቤት

29.እኔ አዲስ መጽሐፍ ገዛሁ። በአርፍተ ነገር ውስጥ የስም ገላጭ የሆነው

ሀ. እኔ ለ. መጽሀፍ ሐ. አዲስ መ. ገዛሁ

30.ከሚከተሉት ውስጥ የጥገኛ ምዕላድ ወይም (ቅጥያ) አገልግሎት የሆነው የቱ ነው

ሀ. የብዙ ቁጥር አመልካች ሐ. ባለንብረትነትን ያመለክታሉ

ለ. ጾታ አመልካች መ. ሁሉም መልስ ነው

31.ከሚከተሉት ሀሣቦች በምህፃረ ቃል የሚፃፈው የቱ ነው

ሀ. የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት ሐ. መሀመድ ሀሰን

ለ. የአፍሪካ ሀገራት መ. ጥበበኛ ሠው

32.መጽሐፌ በሚለው ቃል የተቀጠለው ቅጥያ (ጥገኛ ምዕላድ)---------- ነው

ሀ. - ፌ ለ. ፌ - ሐ. - ኤ መ. ኤ-

33." ካልተቆጣች " በሚለው ቃል ውስጥ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎቹ -------- እና ------- ነው

ሀ.ካ- -ች ለ. ካል- -ች ሐ. ካልቶ- -ች መ. ካ - -ኣች

34. በልብ ወለድ ውስጥ የሰውንም ሆነ የሌላ ባህሪ ወክለው የሚጫወቱ አካላት -------ይባላሉ

ሀ. መቼት ለ. ገፀባህሪያት ሐ. ጭብጥ መ. ትልም

35.*ለይስሙላ* ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ ሊሆን የሚችለው .....ነው

ሀ. ለማስመሰል ለ. እንደነገሩ ሐ. በግዴለሽነት መ. ቁም ነገር

36.አንድ አርፍተ ነገር ማለቁን የሚያመለክት ሥርአተ ነጥብ

ሀ. ሠረዝ ለ. ድርብ ሠረዝ ሐ. ሁለት ነጥብ መ. አራት ነጥብ

37. በርዬ እሹሩሩ
በርዬ እሹሩሩ
የበራን ውለታ
እንጫወት ማታ
በዋንጫ ጋጋታ

ይህ ቃላዊ ግጥም የ---------- ነው

ሀ. የእርሻ ለ. የውቂያ ሐ. የአጨዳ መ. የሠብል ጥበቃ

ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሣሣይ የሚሆነውን መልስ ምረጡ

38.አካያ፡- ሀ. አንዣር ለ. የተከበረ ሐ. የተተወ መ. የደከመ

39.አሸተ፡- ሀ. አሸበረቀ ለ. አሸተተ ሐ. ፍሬ አፈራ መ. ሸፈነ

40.አወሳ፡- ሀ. ጨከነ ለ. አወራ ሐ. አስቀጣ መ. አስወገደ